TAG Treatment Action Group | ascent dr-tb | KNCV TB|PLUS

# መድሃኒትን ስለተለማመደ የሳንባ ህመም የምርመራ ውጤትዎ ከሰዎች ጋር መነጋገር

ጸሃፊ፡ ጀኔፈር ፈሪን     ትርጉም፡ ሊንድሲ ማኬና     መጋቢት 2025

መድሃኒት የተላመደ የሳንባ ህመም(drug-resistant tuberculosis/DR-TB) እንዳለብዎ በምርመራ ከተረጋገጠ በኋላ ሊታሰብበት የሚገባው አንድ አስፈላጊ ጉዳይ በሽታው እንዳለብዎ ለሰዎች እንዴት እንደሚነግሩ ነው። ይህም በህክምናው ሂደት ሰዎች አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉልዎ ለማስቻል ነው። ስለምርመራ ውጤትዎ ለሌሎች የሚነግሩበት ሂደት “ይፋ ማድረግ” ይባላል። የህክምና መረጃን ይፋ ማድረግ ከሰው ሰው ይለያያል፣ እና ውጤትዎን ከማን ጋር እንደሚያጋሩ መወሰን የእርስዎ ሃላፊነት ነው። ይህ መረጃውን ይፋ የማድረግ ሂደት የአንድ ጊዜ ክስተት አለመሆኑን ማስታወስ አስፈላጊ ነው፣ የምርመራ ውጤቱን ይፋ የሚያደርጉት DR-TB እንዳለብዎ ባወቁ በቀናት፣ በሳምንታት ወይም በወራት ጊዜ ውስጥ ሊሆን ይችላል።

## የሚከተሉት ዘዴዎች መድሃኒት የተላመደ የሳንባ ህመም ምርመራ ውጤትዎን ይፋ የማድረጉ ሂደት ምን መምሰል እንዳለበት ለማሰብ ይረዱዎታል

**ሐኪምዎን፣ ነርስዎን ወይም ሌሎች የታመኑ የጤና አገልግሎት ሰጪዎች** ይህንን እንዴት ማድረግ እንደሚችሉ ምክር እንዲሰጡዎት ወይም ይፋ አደራረጉን አብሮውዎ እንዲለማመዱ ወይም እርስዎ የሚፈልጉ ከሆነ መድሃኒት የተላመደ የሳንባ ህመም ምርመራ ውጤትዎን ለሌሎች ሲያሳውቁ አብረዎ እንዲሆኑ ፈቃደኞች መሆን አለመሆናቸውን ይጠይቋቸው።

**በመጀመሪያ የሚያሳውቁት ሰው እንደሚደግፍዎ የሚተማመኑበት ሰው ይሁን።** አብዛኛውን ጊዜ ይህን ማድረግ ከምትተማመኑበት ሰው ወይም ከምትተማመኑባቸው ሰዎች ጋር ሲሆን ቀላል ነው። ይህ ሰው እንደአስፈላጊነቱ ስለ ምርመራ ውጤትዎ ያለውን መረጃ ለሌሎች ይፋ በሚያደርጉ ጊዜ ሊረዳዎ ይችላል።

**ያለብዎትን በሽታ እንዲሁም ህክምናውን ለሌሎች ለማብራራት በቅድሚያ ራስዎ  በትክክል ይረዱ።** የሚታከሙበት ጤና ተቋም ወይም የጤና አገልግሎት ሰጪዎች ስለ DR- TB ለሌሎች ሊያጋሩዋቸው የሚችሏቸው መረጃዎች ሊሰጡዎ ይችላሉ። መድሃኒትን በተለማመደ የ DR- TB ህመም  እና በሌሎች የሳምባ ህመም አይነቶች መካከል ያለውን ልዩነት መረዳትና ለሌሎች ማስረዳት መቻል አስፈላጊ ነው። "መድኃኒት የተለማመደ" የሚለው ቃል የሚገልጸው ለ TB ህመም ህክምና የሚውሉ መድሃኒቶች ኢርስዎ ያለብዎትን የ  TB ህመም አይነት  የማያድኑት መሆኑን ነው። ሆኖም አብዛኞቹን የDR-TB ዓይነቶች ለማከም የሚረዱ መድኃኒቶች አሉ፤ እነዚህ መድሃኒቶች ግን ለረጅም ጊዜ መወሰድ ሊኖርባቸው ወይም የተለያዩ የጎንዮሽ ጉዳቶች ሊያስከትሉ እንደሚችሉ መገንዘብ ያስፈልጋል

**ስለምርመራ ውጤትዎ ማወቅ ያለባቸውን ሰዎች ዝርዝር ያዘጋጁ።** ሁሉም ሰው ስለ መርመራ ውጤትዎ ማወቅ አይኖርበትም፣ የጤና መረጃዎ ግላዊ ነው። ይህንን መረጃ ለማን እንደሚያካፍሉ፣ ምን እንደሚያካፍሉ፣ መቼ እንደሚያካፍሉ እና እንዴት እንደሚያካፍሉ መለየት የእርስዎ ውሳኔ ነው።

**ከመኖሪያ ቦታ፣ ከሥራ ቦታ፣ ከትምህርት ቤትና ሌሎች ማኅበራዊ መገኛዎች ጋር የተያያዙ መብቶችዎን ይወቁ።** ማንኛውም የሚተነፍስ ሰው መድሃኒትን በተለማመደ የሳምባ በሽታ (DR-TB) ሊጠቃ ይችላል፤ በመሆኑም በዚህ በሽታ መያዝዎ ሊያሳፍርዎ ወይም የጥፋተኝነት ስሜት ሊያሳድርብርዎ አይገባም። ስለ ህመምዎ ያወቁ አንዳንድ ሰዎች አሉታዊ ምላሽ ሊሰጡዎ ስለሚችሉ ራስዎን ሚጠብቁበትን እቅድ ማዘጋጀት መልካም ነው።

አ

**ሰዎች (ስለ ህመምዎ ያልነገሯቸው ጭምር) ስለ ጤንነትዎ ቢጠይቁ ምን ማድረግ እንዳለብዎ አስቀድመው ይዘጋጁ፤** ። የDR-TB በሽታ ህክምና ገጽታዎ ላይ አንዳንድ ለውጦችን (ለምሳሌ የክብደት መቀነስ) ሊያመጣ ይችላል። DR-TBን ለማከም ከሚሰጡ መድሃኒቶች መካከልም አንዳንዶቹም የሰውነት ለውጦችን ሊያመጡ ይችላሉ (ለምሳሌ **clofazimine** በቆዳዎ ላይ ለውጦችን ሊያስከትል ይችላል)። ወደ ሆስፒታል ወይም ወደ ክሊኒክ በሚሄዱ ጊዘ ሌሎች በምን ህመም ምክንያት እነዚህ ለውጦች እርስዎ ላይ እንደተከሰቱ እንዲያስቡ ሊያደርጋቸው ይችላል። አንዳንዶች በቀጥታ ሊጠይቁዎ ይችላሉ። ለጥያቄዎች የሚሰጡትን መልስ ቀድመው ማሰብ መቻል መልካም ነው። በአጠቃላይ መናገር የሚፈልጉትን መናገር የእርስዎ ውሳኔ ነው። በቀላሉ ምላሽ የሚሰጡበት አንድ ቀላል ዘዴ ጠያቂዎች ስላሰቡልዎ በማመስገን ጤናዎ ጥሩ ሁኔታ ላይ እንዳለ መግለጽ ነው። አንዳንድ ሰዎች እርስዎን ከመጠየቅ ይልቅ ጓደኞችዎን ወይም የቤተሰብዎን አባላት ሊጠይቁ ይችላሉ፣ ያስታውሱ፣ ከራስዎ በስተቀር ማንም ሰው ስለ ጤናዎ መረጃ የማካፈል መብት የለውም።

**እንደ አካላዊ ጤንነትዎ ሁሉ የአእምሮ ጤንነትዎን ለመንከባከብ የሚያስችሎትን ዘዴዎች ይፈልጉ።** በDR-TB በሽታ መያዝ ለሰውነትዎና ለአእምሮዎ አስጨናቂ ተሞክሮ ሊሆን ይችላል። በዚህ ወቅት ለራስዎ ማሰብ አስፈላጊ ነው። የሳንባ ነቀርሳ በሽታ በአየር ውስጥ በሚገኝ ጀርም የሚከሰት በመሆኑ፤ በበሽታው እንዲያዙ ራስዎ ያደረጉት አስተዋጾ እንደሌለ ያስታውሱ። የሚተነፍስ ማንኛውም ሰው DR-TB ሊይዘው ይችላል። የህክምናዎ ግዜም አስቸጋሪ ጊዜ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ሁሌም አስቸጋሪ ሆኖ ይቀራል ማለት አይደለም። ከሚደግፉዎት ሰዎች ጋር ይሁኑ እና የሚያስደስትዎን ነገር ያድርጉ።

**ሌሎችም ወደ ጤና ተቋም በመሄድ የDR-TB ምርመራ እንዲያደርጉ ያበረታቱ።** በየዓመቱ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በDR-TB ይያዛሉ። ከምንም በላይ ትኩረት ማድረግ ያለብዎ የራስዎን ጤንነት መመለስ ላይ ነው። DR-TB በአየር ውስጥ ስለሚሰራጭ፣ እርስዎ የሚያውቋቸው ሰዎችም በተመሳሳይ አየር ውስጥ የተጋለጡ ሊሆኑ ይችላሉ። በሽታው የያዘው ወይም በሽታው የተገኘበት የመጀመሪያው ሰው እርሶ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ግን ሌሎችም የታመሙ ሊኖሩ ይችላሉ። በፍጥነት ህክምና አገኙ ማለት የመዳን እድልዎ ከፍተኛ ሆነ ማለት ነው። ስለዚህ ምርመራውን ማድረግዎን ሌሎች ሰዎችም ምርመራ እንዲያደርጉ የሚያበረታቱበት ጊዜ አድርገው ሊጠቀሙበት ይችላሉ። የጤና ተቋሙ ወይም የጤና አገልግሎት ሰጪዎች ደግሞ ብዙውን ጊዜ ይህንን ለማድረግ የሚያስችል (የንክኪ መከታተያ) ዘዴ አላቸው። እንደ እርስዎ ተመሳሳይ የትንፋሽ ንክኪ ያላቸው ሰዎችም የቲቢ ምርመራ እንዲያደርጉ እቅድ በማውጣት ሊረዱዎት እና ሊደግፉዎት ይችላሉ ። በዋነኝነት ሌሎች በዙሪያዎ ያሉት ሰዎች የDR-TB ምርመራ እንዲያደርጉ ማድረግ የጤና ስርአቱና የሰዎቹ የራሳቸው ሃላፊነት ነው። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ሰዎች የርስዎን የምርመራ ውጤት ካወቁ በኋላ ወደ ጤና ተቋም በመሄድ በራሳቸው ጤና ዙሪያ ምክር ማግኘት እንደሚችሉ ማሳወቅ መቻልዎ ሂደቱን ያግዛል።

Treatment Action Group

www.treatmentactiongroup.org
90 Broad Street, Suite 2503 New York, NY 10004
Tel 212.253.7922, Fax 212.253.7923

tag@treatmentactiongroup.org